homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ነዋሪ
1 ኤ ሰሪይ ሮድ
ሳውዝ ያራ

ውድ ነዋሪ

ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ታልቁ የቤቶች ግንባታ (Big Housing Build) እድገት እና ስለ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር ለማሳወቅ እየጻፍንልዎት ነው።

የፕሮግራሙ ቀጣይ ምዕራፍ አሁን በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት አሁን በ9 መንደሮች ወይ ሰበርቦች ለሚኖሩ የአሁኑ እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ የሆኑ ቤቶች ወደ ማቅረቡ እያመራን ነው።

የዛሬው ማስታወቂያ በሰፈርዎ ያሉ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል እና ከእነዚህ ነዋሪዎች ጋር በመደበኛነት እንገናኛለን። **ህንጻዎ ወይም በቤትዎ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።**

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና ስለማልማት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፦

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፕራሃን
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

**ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028፣** ወደ ተስማሚ ቤት እንዲሄዱ ለመርዳት ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

## በአቅራቢያዎ አዳዲስ ቤቶችን እየገነባን ነው

የእነዚህን ነዋሪዎች የመዛወር አማራጮችን ለመደገፍ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ቤቶች በአቅራቢያው በግንባታ ላይ ናቸው። በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ኤሴክስ ስትሪት፣ ፕራሃን
- ባራክ ቢኮን፣ ፖርት ሜልበርን
- ሲሞንስ ስትሪት፣ ሳውዝ ያራ
- ሆላንድ ኮርት፣ ፍሌሚንግተን

እነዚህ ቤቶች ለማሞቅ እና ለማቀዝቀዝ ቀላል ይሆናሉ፣ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች የበለጠ ምቹ ይሆናሉ፣ ደህንነትን፣ ብርሃን እና አየር ማናፈሻን ተሻሽሏል እንዲሁም በረንዳዎች እና የግል የልብስ ማጠቢያዎች ይኖራቸዋል።

## በሰፈራችሁ

በ259 ማልቨርን ሮድ፣ ሳውዝ ያራ ላይ ያሉ ጥቂት አባወራዎችን በዝውውራቸው መደገፋችንን እንቀጥላለን።

ወደ 90% የሚጠጉ አባወራዎች ተዛውረዋል፣ ወይም በመዛወር ላይ ናቸው፣ እና ሁሉም እስከ የካቲት 2026 ለመዛወር በሂደት ላይ ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በሲሞንስ ስትሪት እና በኤሴክስ ስትሪት ግንባታዎች ላይ እየተሰሩ ያሉ አዳዲስ ቤቶች እና የማህበረሰብ መገልገያዎች በዚህ አመት ይጠናቀቃሉ። የተሻሻለ ደህንነትን እና ቅድሚያ የአየር ኮንዲሽነር ተከላን ጨምሮ በቀሪዎቹ ማማዎች ላይ የጥገና ፕሮግራማችንን እንቀጥላለን።

## ስለ መልሶ ማልማት ፕሮግራም

የሜልበርን የቆዩ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ዘመናዊ የምቾት፣ የተደራሽነት እና የኃይል (ኢነርጂ) ቆጣቢነት ደረጃዎችን በሚያሟሉ አዳዲስ ቤቶች ይተካሉ።

እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና በማልማት ነዋሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ምቹ እና አሁን እና ወደፊት ለፍላጎታቸው ተስማሚ በሆኑ ቤቶች ውስጥ መኖር እንደሚችሉ እያረጋገጥን ነው።

ሁሉም ነዋሪዎች በአዳዲስ ቤቶች እና በሰፈር ዲዛይን ዕቅዶች ላይ ሃሳብ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ።

## ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስዎ ከኛ ጋር መገናኘትዎ አያቋርጡ

ቤትዎ የሰማይ ጠቀስ ፎቆች መልሶ ማልማት አካል አይደለም፣ ነገር ግን በአካባቢዎ ውስጥ ለውጦች ሲከሰቱ ሊያስተውሉ ይችላሉ። በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ደረጃ ላይ ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ ከእርስዎ ጋር መገናኘታችን አናቋርጥም።

እንዲሁም በአቅራቢያዎ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለማየት እና የቅርብ ጊዜ ዜናዎችን እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመቀበል ለመመዝገብ homes.vic.gov.au ድህረ ገጻችንን መጎብኘት ይችላሉ።

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026